በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
የኮሙኒኬሽንና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምሪያ
በየ15 ቀኑ የሚዘጋጅ ዜና-መጽሔት ቁ.45
Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations
Communication and International Relations Department
Bi-monthly News Letter No.45

# “ጠንካራና ንቁ የሆነ የግሉ ዘርፍ መፈጠር አለበት” የውጭ ጉዳይ ሚንስትር ዶክተር ቴድሮስ አድሓኖም

**.የምክር ቤቱ የዳይሬክተሮች ቦርድና የውጭ ጉዳይ ሚንስትሩ ተወያዩ**

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የዳይሬክተሮች ቦርድ ታህሳስ 12 ቀን 2005 ዓ.ም. ከውጭ ጉዳይ ሚንስትሩ ዶክተር ቴድሮስ አድሓኖም ጋር ትውውቅ በማድረግ በርካታ ጉዳዮችን አንስተው በጥምረት ለመስራት ተስማሙ፡፡



“ጠንካራና ለሀገራችን ኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛና የተሻለ አስተዋፅኦ ማበርከትየሚችል የግል ዘርፍ እንዲፈጠር በደንብ መደገፍ አለብን የሚለው የሚንስቴር መስሪያ ቤቱ አቋም ነው” ያሉት ዶክተር ቴድሮስ የተሻለ ሥራ ለመሥራት ምክር ቤቱና ሚንስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር በየጊዜው እየተገናኙ መወያየት እንደሚገባቸው አፅንኦት ሰጥተው ተናግረዋል፡፡

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በተደረገው የትውውቅ መድረክ የምክር ቤቱ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ንግድና ኢንቨስትመንትን በማስፋፋት፣ የሀገር ገፅታን በመገንባት እና ሌሎች በጥምረትና በትብብር ሊሰሩባቸው ይችላሉ ያሏቸውን ጉዳዮች ለክቡር ሚንስትሩ አቅርበው ተቀባይነት አግኝተዋል፡፡

የምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት ወ/ሮ ሙሉ ሰለሞን እንደተናገሩት ኢትዮጵያ የሀገር ውስጥ ምርቶቿን በውጭ ለማስተዋወቅ በሚደረጉ የውጭ ሀገር ጉዞዎች ላይ የውጭ ጉዳይ ሚንስቴርና ንግድ ምክር ቤቱ ዋንኛ ባለቤት እንደመሆናቸው ምርቶቻችን የትና እንዴት መተዋወቅ አለባቸው? የሚለው ጉዳይ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ መሰራት እንዳለበትና ተጨባጭ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

ፕሬዚዳንቷ አያይዘውም የፓን አፍሪካ የንግድና ኢንዱስትሪ ምክር ቤት ቀድሞ ከነበረበት መቀመጫው ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጣ ከዚህ ቀደም ምክር ቤቱን በአመራርነት ያገለገሉ አካላት የተሳካ ሥራ መሥራታቸውንና ይህም ለሀገራችን ገፅታ ግንባታ ያለውን ጉልህ አስተዋፅኦ አብራርተው የፓን አፍሪካ ምክር ቤት በቀጣይ በሚያከናውናቸው ጉባኤዎችና ተግባራት ኢትዮጵያ ኃላፊነቷን በብቃት እንድትወጣ ሚንስቴር መሥሪያ ቤቱ የበኩሉን ድጋፍ እንዲያደርግ ጠይቀዋል፡፡

በመቀጠልም የንግዱ ህብረተሰብ የንግድ ምክር ቤቶች አባል ሲሆን መሰረታዊ ጠቀሜታ እንዳለውና አባልነት ግዴታ ሆኖ የሚሰራባቸው የሌሎች ዲሞክራሲያዊ ሀገሮችን ልምዶች በማጣቀስ ያብራሩት ወ/ሮ ሙሉ በጉዳዩ ላይ ምክር ቤቱ ጥናት እያደረገ እንደሆነና ለመንግሥት ለማቅረብ እቅድ እንዳለ ተናግረዋል፡፡

የምክር ቤቱ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባልና የኢትዮጵያ የዘርፍ ማኅበራት ፕሬዚዳንት አቶ ገብረሕይወት ገብረእግዚያብሔር በበኩላቸው የሀገራችን ገፅታ ከመገንባቱ አኳያ ገና ብዙ ሥራ አለመሰራቱንና የንግዱ ማኅበረሰብ፣ የሲቪክ ማኅበራት፣ መንግሥት እና ጉዳዩ ያገባኛል ያሉ ድርጅቶች በጥምረት ተንቀሳቅሰው ለዘመናት መገለጫችን ሆኖ የቆየውን ድህነትንና ኋላ ቀርነትን ማስወገድ ይጠበቅብናል ብለዋል፡፡የምክር ቤቱ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል አቶ ሁንልኝ ጥጋቡ በበኩላቸው ኢትዮጵያ የውጭ ሸቀጦች ማራገፊያ ሆና መቀጠል የለባትም ፡፡(ወደ ገፅ 2 ዞሯል)



አድራሻ፣ስ፡ - +251-011-5517699
ኢ-ሜይል: ethchamb@ethionet.et
ደረ-ገጽ፡- www.ethiopianchamber.com

በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
የኮሙኒኬሽንና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምሪያ
በየ15 ቀኑ የሚዘጋጅ ዜና-መጽሔት ቁ.45
Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations
Communication and International Relations Department
Bi-monthly News Letter No.45

በርካታ የጨርቃጨርቅ፣ የአግሮ-ኢንዱስትሪ እና የኮንስትራክሽን ቁሳቁሶች ጭምር እዚሁ መሰራት ሲችሉ ከውጭ እየመጡ ይገኛል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

ዶክተር ቴድሮስ ለተሰጡት አስተያየቶችና ጥያቄዎች ምላሽ ሲሰጡ "የሀገሪቱን ምርቶች በውጭ ለማስተዋወቅ በሚደረጉ ጉዞዎች ንግድ ምክር ቤቶች የተሻለ ልምድ ስላላችሁ ቦታውን የመምረጥ ሀላፊነቱን ለእናንተ እንሰጣለን" ብለዋል፡፡

የንግዱ ማኅበረሰብ አባልነት ግዴታ መሆን አለበት ለምትሉት የሌሎች ዲሞክራሲያዊ ሀገሮች ልምዶችን በተጨባጭ የሚያሳይ የተጠና ፅሁፍ ብታቀርቡ ለማየት እንደሚቻል ተናግረዋል፡፡

ሚንስትሩ የገፅታ ግንባታን በተመለከተ የተሰጠውን አስተያየት አድንቀው እንዴትና በምን መልኩ ወደፊት በጥምረት መስራት እንደሚችሉ አቅጣጫዎችን በጋራ መቀየስ ይገባል ብለዋል፡፡

በተጨማሪም የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤትና የውጭ ጉዳይ ሚንስቴር እ.አ.አ በሜይ 2013 ዓ.ም. በሚከበረው የአፍሪካ ኅብረት 50ኛ ዓመት የምስረታ በዓል ላይ የግሉ ዘርፍ መወከል እንዳለበትና ይህም የተሳካ እንዲሆን ሁለቱ መሥሪያ ቤቶች ከወዲሁ ዝግጅት እንዲያደርጉ መግባባት ላይ ደርሰዋል፡፡

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ከቀድሞው የውጭ ጉዳይ ሚንስትር እና ምክትል ጠቅላይ ሚንስትር አቶ ኃይለማሪያም ደሳለኝ ጋር ተመሳሳይ የትውውቅና አብሮ የመሥራት መድረክ ፈጥረው እንደነበር የሚታወስ ሲሆን ዶክተር ቴድሮስ ቦታውን ሲረከቡ የተደረጉት ስምምነቶች እንዲቀጥሉ የትውውቅ መድረኩ መካሄድ እንዳለበት ሀሳቡ የቀረበው ከክቡር ጠቅላይ ሚንስትር ኃይለማሪያም ደሳለኝ እንደሆነ ዶክተር ቴድሮስ ተናግረዋል፡፡

## የሀዋሳ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የምክክር መድረክ አዘጋጀ .የራሱን ህንፃ ሊገነባ ነው

የሀዋሳ ከተማ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ታህሳስ 9 ቀን 2005ዓ.ም. የንግዱን ማኅበረሰብ ከመንግሥት ጽ/ቤቶች አመራር አካላት ጋር በማቀራረብ አልፎ አልፎ በመሀከላቸው የሚከሰቱ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል የውይይት መድረክ አዘጋጀ፡፡

የምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት አቶ ወሌ አበጋዝ በተለይ ለኢትዮ-ቻምበር እንደገለፁት ነጋዴው ከመንግሥት ጋር ተራርቆ ያለበት ሁኔታ እንዳለና የንግዱ ኅብረተሰብ መንግሥትን በጥርጣሬና በፍርሀት እንደሚመለከተው እንዲሁም መንግሥትም በንግዱ ኅብረተሰብ ላይ ያለው አመኔታ አናሳ መሆኑን የገለፁ ሲሆን ሁለቱ አካላት በትብብር በመስራት በመሀከላቸው ያለውን የጥርጣሬና ያለመተማመን መንፈስ ማስወገድ እንዳለባቸው መግባባት ላይ ደርሰዋል ብለዋል፡፡

በተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም(UNDP) የገንዘብ ድጋፍ በሀዋሳ ሴንትራል ሆቴል ከክልሉ ገቢዎችና ጉምሩክ፣ ከንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ እንዲሁም ከሌሎች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሀላፊዎች ጋር የተደረገው ውይይት መንግሥት በንግዱ ማኅበረሰብ ይታያሉ ያላቸውን ችግሮች በዝርዝር ያስቀመጠበት እንዲሁም የንግዱ ማኅበረሰብ ከመንግሥት ተገቢውን አገልግሎቶች ማግኘት ያልቻሉባቸውን ጉዳዮች በግልፅ ያነሱበት፣ በጥሩ መግባባትና በሰከነ መንፈስ የተደረገ ስኬታማ የውይይት መድረክ ነበር ሲሉ አቶ ወሌ ተናግረዋል፡፡

ከመንግሥት በኩል ከተነሱ ችግሮች መሀከል የንግዱ ህብረተሰብ የግብር ስርዓቱን ተከትሎ በህጋዊ መንገድ የመሥራት ችግር እንዳለበት በአፅንኦት የተገለፀበት ሁኔታ እንደነበር የገለፁት አቶ ወሌ የንግዱ ህብረተሰብም በበኩላቸው ሸቀጦችን ከሚያመጡበት ከአዲስ አበባ ደረሰኝ የማግኘት እና ተዛማጅ ችግሮች እንደሚገጥሟቸው ተናግረዋል፡፡

ሀያ አምስተኛ ዓመት የምስረታ በዓሉን ከወራት በኋላ ለማክበር በዝግጅት ላይ ያለው የሀዋሳ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት 1640 አባላት ያሉ ሲሆን የራሱን ጽሕፈት ቤት ለመገንባት መሬት ተረክቦ እንቅስቃሴዎች መጀመሩ ለመረዳት ተችሏል፡፡

አድራሻ፡ስልክ: - +251-011-5517699
ኢ.ሜይል: ethchamb@ethionet.et
ደረ-ገጽ:- www.ethiopianchamber.com

በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
የኮሙኒኬሽንና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምሪያ
በየ15 ቀኑ የሚዘጋጅ ዜና-መጽሔት ቁ.44
Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations
Communication and International Relations Department
Bi-monthly News Letter No.44

# የኢራን የንግድ ልዑካን አዲስ አበባ ሊመጡ ነው

የኢራን ኢስላማዊ ሪፓብሊክ የንግድ ልዑካን በየካቲት ወር 2004 ዓ.ም. ለአንድ ሳምንት የሚቆይ የሥራ ጉብኝት ለማድረግ በአዲስ አበባ እንደሚቆዩ በኢትዮጵያ የኢራን አምባሳደር አሊ ባህሬይን ገለፁ፡፡

አምባሳደሩ ከምክር ቤቱ ዋና ፀሀፊ አቶ ጋሻው ደበበ ጋር ታህሳስ 10 ቀን 2004ዓ.ም. ጋር ባደረጉት ውይይት ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡት የኢራን የንግድ ልዑካን በሀገሪቱ እጅግ ስኬታማ የሚባሉ የኢንጅነሪንግ ኩባንያዎችን ያካተተ ሲሆን በተለይ ለኢትዮጵያ የኢነርጂ ፍላጎት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማበርከት ይችላሉ ብለዋል፡፡

አምባሳደሩ አያይዘውም የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ልዑካን ወደ ኢራን ዋና ከተማ ቴህራን ሄደው የሀገሪቱን ንግድ ምክር ቤት እንዲጎበኙ ጥሪ ያቀረቡ ሲሆን በሁለቱ ሀገራት ምክር ቤቶች መሀከል የመግባቢያ ሰነድ እንዲፈረም ሀሳብ አቅርበዋል፡፡

የምክር ቤቱ ዋና ፀሐፊ አቶ ጋሻው በበኩላቸው አምባሳደሩ የሁለቱ ሀገሮችን ንግድ ምክር ቤቶች ለማቀራረብ ያሳዩትን ተነሳሽነት አድንቀው በሀገራቱ መሀከል ለሚደረጉ የንግድ ለንግድ ስምምነቶች ምክር ቤቱ ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሰራ ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያ ለኢንቨስትመት አመቺ የሆነች ሀገር እንደሆነች የገለፁት አቶ ጋሻው የኢራን የንግድ ልዑካን በኢትዮጵያ ሊሰማሩባቸው የሚችሉባቸው በርካታ የኢንቨስትመንት መስኮች እንዳሉም አያይዘው ገልፀዋል፡፡

## የኢንዱስትሪውን ዘርፍ ለማሳደግ የተቀናጀ ጥረት እንደሚያስፈልግ ተገለፀ

.የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ሳምንት ለ12ኛ ጊዜ ተከበረ

በናሽናል አሶሲዮሽን ኦፍ ኢትዮጵያን ኢንደስትሪስ አዘጋጅነት ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ ላለፉት አሥራ አንድ ዓመታት ሲከበር የቆየው የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ሳምንት ዘንድሮም ለ12ኛ ጊዜ ከታህሳስ 4-11 ቀን 2005 ዓ.ም በልዩ ልዩ ዝግጅቶች ተከበረ፡፡

የኢንዱስትሪ ሳምንቱን ምክንያት በማድረግ “ተግባራዊ ምርምር እና ጥናት ለኢንዱስትሪ ዕድገት” በሚል መሪ ሃሳብ የፓናል ውይይት በታህሳስ 9 ቀን 2005 ዓ.ም በራስ ሆቴል አዳራሽ የተካሄደ ሲሆን የእንኳን ደህና መጣችሁ መልእክት ያስተላለፉት የአሶሲዮሽኑ የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ አቶ መሐመድ ኑር ሳኒ እንደተናገሩት ለ12ኛ ጊዜ በመከበር ላይ ያለው በዓል መነሻ ያደረገው መንግስት በዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መጨረሻ ኢንዱስትሪው ከግብርናው ዘርፍ የኢኮኖሚ መሪነት ሚናውን እንዲረከብ ለማስቻል የሰጠው ልዩ ትኩረት መሆኑን አስረድተዋል፡፡ በመሪ ሃሳቡ ይህንን መልዕክት እንዲንፀባረቅ የተደረገው ኢንዱስትሪው የተጣለበትን ብሔራዊ ሃላፊነት በብቃት መወጣት ይችል ዘንድ በዘርፉ የሚታዩትን ችግሮች በመለየት የተሻለ ሁኔታን ለመፍጠር እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

ችግሮች በመለየት የተሻለ ሁኔታን ለመፍጠር እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ውይይቱን በንግግር የከፈቱት የኢትዮጵያ የንግድ እና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ወ/ሮ ሙሉ ሰሎሞን በበኩላቸው ኢትዮጵያ በከፍተኛ ፍጥነት እያደጉ ካሉ ሀገሮች አንዷ መሆንዋን አስታውሰው ሀገሪትዋ ያላትን የተፈጥሮ ሀብት ለመጠቀም የሚያስችል ፖሊሲዎችና እስትራቴጂዎች በመንደፍ ከፍተኛ የኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲኖር በምታደርገው ጥረት በኢንዱስትሪው፤ በግብርናው እና በአገልግሎት ዘርፍ እያስመዘገበች ያለችው እድገት ከዓመት ዓመት እየጨመረ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

አድራሻ፥ስ፡ - +251-011-5517699
ኢ.ሜይል: ethchamb@ethionet.et
ደረ-ገጽ፡- www.ethiopianchamber.com

ተጨማሪም የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ወደ አምራችነት እየተሸጋገሩ እንዲሁም የግብርና ውጤቶች ወደውጭ በጥሬው ከመላክ ይልቅ እሴት ተጨምሮባቸው የተሻለ ገቢ እንዲያስገኙ እየተደረጉ ያሉት ጅምር ስራዎች አበረታች መሆናቸውን ጠቅሰው ባጠቃላይ ሀገሪትዋ እያስመዘገበችው ባለው የማህበረ - ኢኮኖሚ እድገት የግሉ ዘርፍ ከፍተኛ ድርሻ ይዞ እንደሚገኝ አስረድተዋል፡፡

ወ/ሮ ሙሉ አክለውም በዓለም አቀፍ ደረጃ እጅግ ተፈላጊ የሆኑ የግብርና ውጤቶችን ለዓለም ገበያ ማቅረብ የምትችለው ሀገራችን የሚጠበቀውን ያህል የውጭ ምንዛሪ እያገኘች እንዳልሆነ ገልፀው ለዚህም የኢንዱስትሪ እና የማኒፋክቸሪንግ ዘርፉ ገና ያልዳበረ እና በብዙ ችግሮች የተተበተበ በመሆኑ እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡

ዓለማችን በከፍተኛ ፍጥነት ወደ ትንሽ መንደር እየተለወጠች ነው ያሉት ወ/ሮ ሙሉ የዓለም ሀገራት በየቀጠናቸውና አህጉራቸው ሀገራትን የሚያስተሳስሩ የተለያዩ ፖለቲካዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ስምምነቶችን እየቀረፁና እየተገበሩ ይገኛሉ ብለዋል፡፡ እነዚህ የንግድ ስምምነቶች የኢኮኖሚ ትስስርን በማጎልበት የተሻለ የኢኮኖሚ እድገትን በመፍጠር የየሀገራቱን እድገት የሚያፋጥኑ እንደሆኑ ተስፋ የተደረገባቸው እንደሆነ ገልፀው ስምምነቶቹ ድንበር ዘለል ነፃ የገበያ ቀጠና (Free Trade Area) በአባል ሀገራት የሚፈጥሩ መሆናቸውን አስታውሰዋል፡፡

በአፍሪካም ሶስት የንግድ ቀጠናዎች መመስረታቸውን ፕሬዚዳንቷ አስታውሰው ሶስቱም ቀጠናዎች እንዲሁ የሶስትዮሽ ስምምነት በመላው አፍሪካ ነፃ የገበያ ቀጠናውን ለመተግበር የሚያስችል ስምምነት መፈረማቸውንና በስምምነቱ መሰረትም እ.ኤ.አ. በ2017 ሁሉም የቀጠናው አባል ሀገራት ነፃ የገበያ ቀጠናውን ለመቀላቀል መስማማታቸውን ገልፀዋል፡፡

የሀገራችን የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ በዚህ ውድድር ውስጥ ገብቶ በአሸናፊነት መውጣት መቻል አለበት ያሉት ፕሬዚዳንቷ በአሸናፊነት እንዲወጣም በጥናትና በምርምር እየታገዘ በዕቅድ ላይ የተመሠረተ ሥራ እንዲሠራ ይጠበቃል ብለዋል፡፡

ስለሆነም የግሉ ዘርፍ የተፈለገውን ውጤት እንዳያመጣ ማነቆ የሆኑትን ችግሮች በመቅረፍ እና ለማኑፋክቸሪንግ እና ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፎች የተለየ ድጋፍ በማድረግ አገሪቱ በግብርና ጥገኛ መሆንዋ ቀንሶ ወደ ኢንዱስትራላይዜሽን የምትሸጋገርበትን ዕድል መክፈት እንደሚያስፈልግ ገልጣ በዚህ በኩል ከመሥሪያ ቦታ፤ በጥሬ ዕቃ ላይ ከሚከፈል ግብርና ታክስ፤ በልምድ ልውውጥ ፕሮግራሞች ተሳትፎና በመሳሰሉት መንግስት ድጋፍ ሊያደርግ እንደሚገባ ሳይጠቁሙ አላለፉም፡፡

የበዓሉ ዋና ዓላማ በኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ዕድገት ላይ ትኩረት ሊሰጣቸው ከሚገቡ ጉዳዮች ውስጥ በዋናነት ባለ ኢንዱስትሪው፤ መንግስት፤ ህብረተሰቡ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማስቻል ነው፡፡

